በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

ሚያዝያ/2017 ዓ.ም.

ማውጫ

የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ————-—1

የኢፌዴሪ ጠ/ሚኒስትር በፒ4ጅ————--1

ለትግራይ ፕሬዚዳንት የእንኳን ደስ አለዎት መልዕክት————————-————---2

የፕሬዚዳንቱ መልዕክት በፒ4ጅ ዙሪያ--2

የምክር ቤቱ ልዑክ በቬትናም ———2

የፒ4ጅ የሚኒስትሮች ስብሰባ -———3

ም/ቤቱ ከቬትናም ኩባንያዎች ጋር—-3

ም/ፕሬዚዳንቱና የእስራኤል ተወካዮች-4

በቬትናም የኢኖቬሽን ስብሰባ ———-4

የሐዘን መግለጫ ————————-4

የኢትዮ ሳኡዲ ስብሰባ ————5-6

የኦሮሚያ ን/ዘ/ማ/ም/ቤት ቦርድ—-7

የUNODC ስልጠና ቢሾፍቱ————7

በጣሊያን ሬሚኒ ኤክስፖ————8

ቢዝነስ ፎረም በአቡዳቢ————-9

ኮሜሳ የንግድ ትርኢት————9

ኢትዮ-እስራኤል ፎረም ———-10

ከECOTRADE ውይይት———11

ስልጠና ለሰራተኞች ————-12

የኢንዘማም/ቤት————-13

አድራሻ————————-14

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ 1ኛ ዓመት 4ኛ መደበኛ ስብሰባውን በአዲስ አበባ ኢሊሊ ሆቴል አካሄደ ።።



ቦርዱ የ2017 በጀት ዓመት የ3ኛውን ሩብ ዓመት እቅድ አፈጻጸም በመገምገምና በሌሎችም ጉዳዮች



ዙሪያ ተወያይቶ ስብሰባውን አጠናቋል። በተለያዩ ጉዳዮች





ዙሪያ ውሳኔዎችን አሳልፏል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በ2025 ፒ4ጂ ቬይትናም ጉባኤ

“ዘላቂ እና ሕዝብን ማዕከል ያደረገ አረንጓዴ ሽግግር” በሚል ጭብጥ እየተካሄደ ባለው የ2025 ፒ4ጂ ቬይትናም ጉባኤ የአየር ንብረት ጥበቃን ለማራመድ አስፈላጊ የሆኑ ሶስት ቁልፍ የተግባር ነጥቦችን አፅንዖት ሰጥቼ አንስቻለሁ። አንደኛ የአየር ንብረት ጥበቃ የገንዘብ አቅርቦትን የቅድሚያ ቅድሚያ በመስጠት በቂ፣ ተገማች እና ዘላቂ በሆኑ ምንጮች ማረጋገጥ ይኖርብናል። ሁለተኛ ዘላቂ ልማትን ለመደገፍ እና የአጎጉሩን ወሳኝ ሥነምኅዳር ጥበቃ ለማድረግ በአለም የኃይል ምንጭ ኢንቬስትመንት ሽፋን ውስጥ የአፍሪካን ድርሻ በአሁኑ ወቅት ካለበት ሁለት ከመቶ በ2030 ወደ ሃያ ከመቶ ማሳደግ ይገባናል።





ሶስተኛ የብዝኀ ሕይወት ጥፋትን እና የምድር መራቆትን በመዋጋት ተፈጥሮን ለመጠበቅ አፋጣኝ ርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል። ይኽም እንደ አረንጓዴ አሻራ ያሉ ሕዝባዊ ሥራዎችን በገንዘብ መደገፍን በዚህም ለየአካባቢው ኅብረተሰብ ከአድልዎ የፀዳና ፍትኀዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን ያካትታል ብለዋል።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ሌተናል ጄኔራል ታደሰ ወረደ የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት ሆነው በመመረጣቸው የእንኳን ደስ ያሎት መልዕክት አስተላለፉ።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ሌተናል ጄኔራል ታደሰ ወረደ የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት ሆነው በመመረጣቸው የእንኳን ደስ ያሎት መልዕክት አስተላለፉ።





ፕሬዚደንቱ በመልዕክታቸው ሌተናል ጄኔራል ታደሰ ወረደ የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት ሆነው በመመረጣቸው የተሰማኝን ደስታ እየገለፅኩኝ የእርሳቸው መመረጥ ለአካባቢው ብሎም ለአገራችን ከሚኖረው ትልቅ ፋይዳ አንጻር ዳግም በተስፋ ተሞልቻለው ብለዋል።

አክለውም እርስዎ ፦

ፈተናዎችን የሚሻገሩበት እንዲሁም የትግራይን ብልጽግና የሚያረጋግጡበት መልካም የስራ ጊዜ እንዲሆንልዎት ፤

በእርስዎ የአስተዳደር ዘመንም ሰላም ወዳዱና ሰላም የናፈቀው የክልሉ የንግዱ ማህበረሰብ ወደ ቀድሞ የንግድ እንቅስቃሴው የሚመለስበትና የአገራዊ ለዉጡን ትሩፋት የሚቋደስበት ሰላሙንም የሚያጸናበት እንዲሆን እመኛለው

በተጨማሪም መላው የክልሉ የንግድ ማኅበረሰብ ከእርስዎ አመራር ጋር በመሆን የትግራይን ብልጽግና እንዲያረጋግጥ ጥሪዬን አቀርባለው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የግሉ ዘርፍ ለዘላቂ እና ህዝብን ላማከለ አረንጓዴ ሽግግር ስኬታማነት የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ጥሪ አቀረቡ።

ፕሬዘዳንቱ በመልዕክታቸው " ዘላቂ እና ህዝብን ያማከለ አረንጓዴ ሽግግር" በሚል መሪ ቃል በቬትናም እየተካሄደ ያለው የ2025 ፒ4ጂ የቬትናም ጉባዔ በጠቅላይ ሚንስትር አብይ አህመድ (ዶ/ር) የመክፈቻ ንግግር መጀመሩንና የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ምህበራት ምክር ቤት ልዑክም በዚህ ወሳኝ ጉባዔ ላይ ተሳትፎ እያደረገ ስለመሆኑ ገልፀዋል።







አክለውም በስብሰባው የብዝሀ ህይወት መጥፋት እና የመሬት መራቆትን በመታገል ተፈጥሮን ለመጠበቅ አስቸኳይ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት እና እንደ አረንጓዴ አሻራዎች ያሉ የህዝብ ስራዎችን በገንዘብ መደገፍ እንዲሁም የብዝሀ ህይወት ለአካባቢው ማህበረሰቦች ፍትሃዊ ጥቅሞችን ብቻ የሚያስገኙ ከመሆናቸው አንፃር ሊበረታቱ እንደሚገባ አፅንኦት ተሰጥቶበታል ብለዋል።

በዚህ አጋጣሚም ምክር ቤታችን ለዘላቂ እና ህዝብን ላማከለ አረንጓዴ ሽግግር ስኬታማነት ያለውን ቁርጠኝነት እየገለፀ ፤ የግሉ ዘርፍም የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ጥሪዬን አቀርባለው ሲሉ አጠቃለዋል።

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ቀነኒሳ ለሚ (ዶር) የተመራው የኢትዮጵያ የንግድ ምክር ቤት ልዑክ በቬትናም የስራ ጉብኝት አድርጓል::





በሥራ ጉብኝቱም ፤ ኢትዮጵያ አረንጓዴ ልማትን እና ሁሉን አቀፍ ልማትን ለማስፋፋት ከተነሱ አለም አቀፍ አጋሮች ጋር ያላትን ትብብር እንዲሁም ቁርጠኝነት ያሳየችበት ነው:: በንግድና ኢንቨስትመንት ፎረሙ ላይ ኢትዮጵያ ለዘላቂ ኢኮኖሚ እድገት ያላትን ቁርጠኝነት እና ለአየር ንብረት ለውጥ መቋቋም እና አረንጓዴ ልማት ሽግግርን ለማጎልበት በአለም አቀፍ አጋርነት ላይ ያላትን የነቃ ተሳትፎ አጎልቶ ያሳየ ተሳትፎም አድርጋለች ። ፎረሙ አረንጓዴ ልማትን እና ሁሉን አቀፍ አገራዊ ልማትን ለማስፋፋት ከተነሱ አለም አቀፍ አጋሮች ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችል አዳዲስ እድሎችን ለአገራችን ፈጥሯል::

የፒ 4 ጂ ጉባዔ “ዘላቂ እና ሕዝብን ያማከለ አረንጓዴ ሽግግር” በሚል መሪ ቃል የተካሄደ ከፍተኛ የሚኒስትሮች ስብሰባ

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በ2025 በቬትናም በተካሄደው የፒ 4ጂ ጉባዔ አካል “ዘላቂ እና ሕዝብን ያማከለ አረንጓዴ ሽግግር” በሚል መሪ ቃል በተካሄደ ከፍተኛ የሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ተሳትፏል።




የሚኒስትሮች ስብሰባ በኢትዮጵያ እና ቬትናም መካከል ያለውን ዓለም አቀፍ ትብብር ለማጎልበት እና የንግድ እና የኢንቨስትመንት እድሎችን ለማጎልበት ወሳኝ መድረክ ሆኖ አገልግሏል፤ ይህም ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ የአረንጓዴ ልማት ላይ ያተኮረ ነው።



የግብርና ሚኒስትru ዶ/ር ግርማ አመንቴ በንግግራቸው ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ያላትን ቁርጠኝነት አብራርተዋል።

በአረንጓዴው ሽግግር የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማመቻቸት አስፈላጊ መሆኑንም አመልክተዋል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የንግድ ማህበረሰብን በመወከል የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሀፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ተገኝተዋል።



በውይይቱ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ የድርጅቶች ተወካዮች እና የመንግስትና የግሉ ሴክተር ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

አዳዲስ የንግድና ኢንቨስትመንት ኮሪደሮችን ለመክፈት፣ አረንጓዴ ፋይናንስን በማንቀሳቀስ እና ሰዎችን እና ፕላኔቷን በሚያስቀድሙ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ልምዶች ላይ ተሞክሮዎችን በመለዋወጥ ላይ ያተኮረ ውይይት ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተሳትፎ ዘላቂ ልማትን በማስፈን እና የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ ትርጉም ባለው መልኩ ከኢትዮጵያ የአየር ንብረት ፍላጎት እና የኢኮኖሚ ለውጥ አጀንዳ ጋር በሚጣጣሙ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ እንዲሳተፍ ሚናውን የሚያሳይ ነው።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከቬትናም ኩባንያዎች ጋር የንግድና ኢንቨስትመንት ውይይት

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከቬትናም ኩባንያዎች ጋር ከፍተኛ የንግድና ኢንቨስትመንት ውይይት አካሄደ።

ውይይቱ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት ትብብር ማሳደግ ላይ ያተኮረ ነው።



በስብሰባው ላይ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር), በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፖሲፊክ እና እስያ ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ንጉስ ከበደ ከተለያዩ ሴክተሮች የተውጣጡ በርካታ የንግድ መሪዎችና ባለሀብቶችም ታድመዋል።



ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ በንግግራቸው ኢትዮጵያ ያላትን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታዎች



ማለትም ጥቅም ላይ ያልዋሉ የተፈጥሮ ሃብቶች፣ የወጣት የሰው ሃይል፣ መሠረተ ልማት መስፋፋት እና የፖሊሲ ምኅዳሩን ከጊዜ ወደ ጊዜ ኢንቨስትመንትን የሚደግፍ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በማኑፋክቸሪንግ፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በማእድን፣ በቱሪዝም እና በታዳሽ ሃይል ዘርፎች ኢንቨስትመንትን ቅድሚያ ሰጥታ እየሰራች መሆኑንም አጽንኦት ሰጥተዋል።



"የቬትናም ባለሀብቶች በኢትዮጵያን እያደገ ያለውን ገበያ እና በተለያዩ ዘርፎች የምንሰጣቸውን ተስፋ ሰጪ እድሎች እንዲያማትሩ አስገንዝበዋል።

ዶ/ር ቀነኒሳ አያይዘውም ምክር ቤቱ የግሉ ዘርፍ ግንባር ቀደም ተቋም እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያውያን እና የቬትናም ቢዝነሶች ድልድይ ሆኖ ለማገልገል፣ የጋራ ልማትን የሚያበረታታ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የጋራ እድገትን የሚደግፉ የእውቀት ልውውጥ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር አይናለም አባይነህ ከእስራኤል መንግሥት ተወካዮች ጋር ተወያይተዋል።



በኢትዮጵያ እና የአፍሪካ ህብረት የእስራኤል ምክትል አምባሳደር ቶመር ባር-ላቪ እና በእስራኤል የኢኮኖሚና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የወጭ ንግድ አስተዳደር እና በናይሮቢ የእስራኤል የኢኮኖሚ ሚሽን ኃላፊ ሚስተር ባራክ ግራኖት ተገኝተዋል።



ሁለቱ ወገኖች በሁለቱ ሀገራት የንግድ ፣ የኢንቨስትመንት እና የኢኮኖሚ ትብብር ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል። የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላቸው በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የኢኮኖሚ አጋርነት፣ ኢንቨስትመንት እና የንግድ ልውውጥ ትልቅ እድል መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑም ተነስቷል።



በውይይቱ ወቅት እንደተገለፀው የሁለቱ ሀገራት ንግድ ምክር ቤቶች ለሁለቱም ሀገራት የንግድ ስራ ምቹ ሁኔታዎችን የማስተዋወቅ አቅም አላቸው።

በቬትናም በተካሄደው የፒ 4 ጂ ጉባኤ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት በኢኖቬሽን እና ዘላቂነት ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ ተካሂዷል።



በዚህም የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)ን ጨምሮ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች የተሳተፉበት ነው።

ስብሰባው ተጽእኖ ፈጣሪ አለምአቀፍ ተዋናዮችን በማሰባሰብ በተለያዩ ዘርፎች ዘላቂነት ያለው ለውጥ ለማምጣት እና ትብብርና ትስስርን ለማጠናከር የመንግስ እና የግሉን ዘርፍ የተሻለ ግንኙነት ለማምጣት የሚያስችል ነው።



ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚም የተባበሩት መንግስታት የኢኮኖሚ እና ልማት ድርጅት ዋና ጸሐፊን ጨምሮ አምባሳደሮችን፣ የአለም አቀፍ ድርጅቶች መሪዎችን እና የአለም አቀፍ የግሉ ሴክተር ከፍተኛ ተወካዮችን ባካተተው ልዩ ጉባኤ ነው የተሳተፉት።

ፎረሙ የዘርፍ ተሻጋሪ ትብብር አረንጓዴ ትራንስፎርሜሽን፣ ዘላቂ ልማትን እና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገትን ማፋጠን በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ወሳኝ የውይይት መድረክ በመሆን ፋይዳው የጎላ ነው።

የሐዘን መግለጫ

የቀድሞው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰሎሞን አፈወርቅ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።



አቶ ሰሎሞን አፈወርቅ ከሚያዝያ/2006 እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት በመሆን ያገለገሉ ሲሆን፤ ባደረባቸው ህመም በህክምና ሲረዱ ቆይተው ሚያዝያ 9 ቀን 2017 ዓ.ም አርፈዋል።

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ስም በአቶ ሰሎሞን አፈወርቅ ህልፈተ ሕይዎት የተሰማኝን ጥልቅ ሐዘን እየገለጽኩኝ ለቤተሰቦቻቸው እና ወዳጅ ዘመዶቻቸው ሁሉ መጽናናትን እመኛለው።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት

ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር

የኢትዮ - ሳዑዲ የጋራ ንግድ ምክር ቤት ስብሰባ በሳኡዲ ርዕሰ ከተማ ሪያድ ተካሄደ::

የኢትዮ - ሳዑዲ የጋራ ንግድ ምክር ቤት የመጀመሪያው ስብሰባ ተካሄደ።

ስብሰባው በኢትዮጵያ ወገን የንግድ ም/ቤቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ሃሰን አብዱላሂ እና በሳዑዲ ወገን የጋራ ም/ቤቱ ሊቀመንበር አብዱላህ አላጅሚ በጋራ የተመራ ሲሆን በውይይቱም በሁለቱ አገራት ያለውን ታሪካዊ ግንኙነት በማውሳት ይህንንም በኢኮኖሚው ዘርፍ ማጠናከር እንደሚገባ ተገልጿል።



መድረኩ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ታሪካዊ ትስስር የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን አዲስ የኢኮኖሚ ትብብር እና የስትራቴጂክ አጋርነት ምዕራፍ የሚያመጣ እንደሆነ በውይይቱ ተነስቷል።



በስብሰባው የሁለቱን አገራት የኢኮኖሚ ትብብር ለማጠናከር እንዲያስችል በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ፣ በግብርና፣ በማዕድን ፣ በቱሪዝም እና በኮንስትራክሽን ዘርፎች አብሮ ለመስራት ተስማምቷል።(በሪያድ የኢትዮጵያ ኢምባሲ)

በፎረሙ ላይ ከ100 በላይ የሁለቱ አገሮች የንግድ ማህበረሰብ አባላትን የመንግስት የስራ ሃላፊዎች የተገኙ ሲሆን፥ በሁሉቱም አገሮች ለንግዱ ማህበረሰብ ያሉ መልካም እድሎችን በተመለከተ ገለጻዎች ተደርገዋል፥ በንግዱ ማህበረሰብ አባላት መካከልም የቢ2ቢ ውይይቶች ተካሂደዋል።(በሪያድ የኢትዮጵያ ኢምባሲ)



የኢትዮ-ሳዑዲ የጋራ ንግድ ም/ቤት የመጀመሪያ ስብሰባ እና የቢዝነስ ፎረም ሚያዚያ 14 ቀን 2017 በሳዑዲ አረቢያ ዋና ከተማ ሪያድ ተካሄዷል።

ስብሰባው በኢትዮጵያ ወገን በኢፌዴሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ በክቡር ዶ/ር አብዱልሃኪም ሙሉ እና በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የተመራ ሲሆን የሳዑዲ አረቢያን ልኡካን የሳኡዲ አረቢያ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሃሰን ቢን ሙጂብ አልሁዋዚ መርተዋል።



በፎረሙ ላይ የኢፌዴሪ ልዩ መልዕክተኛ እና ባለ ሙሉ ስልጣን አምባሳደር ክቡር ዶ/ር ሙክታር ከድርና የኤምባሲው ባልደረቦች፤ የሁለቱ አገራት የንግድ ምክር ቤቶች የዴሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ስራ ኃላፊዎች፤ ከ150 በላይ የሁለቱ አገሮች የንግድ ማህበረሰብ አባላትና የመንግስት የስራ ሃላፊዎች የተገኙ ሲሆን፥ በሁሉቱም አገሮች ለንግዱ ማህበረሰብ ያሉ መልካም እድሎችን በተመለከተ ገለጻዎች ተደርገዋል፥ በንግዱ ማህበረሰብ አባላት መካከልም የቢ2ቢ ውይይትም ተካሂዷል



ኢትዮ ሳኡዲ —የቀጠለ

በሌላ በኩል የኢትዮ-ሳዑዲ የጋራ ንግድ ም/ቤት የመጀመሪያ ስብሰባ እና የቢዝነስ ፎረም ተካሄዷል።



በስብሰባው ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር መድረኩ በሁለቱም አገራት ያለውን የንግድና የኢንቨስትመንት እድልን ያጎለብታል ሲሉ ተናግረዋል።

በሳኡዲ ወገን በኩል በ2030 የሳዑዲ አረቢያ ሁለንተናዊ እድገት ራዕይ የአፍሪካን አህጉር በኢኮኖሚው ዘርፍ ዋና መዳረሻ ያደረገ እንደሆነና ኢትዮጵያን ስትራቴጂካዊ የንግድና ኢንቨስትመንት አጋር በማድረግ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጡ አብራርተዋል።

ውይይቱ በሁለቱ አገሮች መካካል ያሉ የንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም እድሎችን እየለየና የሚያጋጥሙ ችግሮችን እየፈታ በመስኮቹ የሚኖሩ ትብብሮችን እንደሚያጎለብት የተገለፀ ሲሆን፣ የቢዝነስ ፎረሙ የቀረቡ ሃሳቦችና የንግድ ማህበረሰብ መካከል የተደረጉ



ውይይቶች እጅግ ጠቃሚ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል። ፎረሙ በግንቦት 2016 ዓ.ም በሁለቱ አገሮች ንግድ ምክር ቤቶች መካከል በተፈረመው የመግባቢያ ስምምነት መሰረት የተካሄደ ሲሆን፣ በቀጣይ አመት አዲስ አበባ ላይ የሚካሄድ መሆኑም ታውቋል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር በሳዑዲ አረቢያ ዋና ከተማ ሪያድ የመጀመሪያው ስብሰባና የቢዝነስ ፎረም በተሳካ ሁኔታ ተጀምሮ እንዲጠናቀቅ ክትትል እና ድጋፍ ላደረጉ ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ፣ ለኢፌዴሪ የውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ፣ በኢትዮጵያ የሳዑዲ ኤምባሲ፣ በሳዑዲ አረቢያ የኢፌዴሪ ልዩ መልዕክተኛ እና ባለ ሙሉ ስልጣን አምባሳደር ክቡር ዶ/ር ሙክታር ከድርና ለኤምባሲው ባልደረቦች እንዲሁም የሳኡዲ አረቢያ የንግድ ምክር ቤቶች ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት ሃሰን ቢን ሙጂብ አልሁዋዚ እና ባልደረቦቻቸው፣ የ ፕሮግራሙ ድምቀት የነበራችሁ የልዑካን ቡድን አባላት ፣ ለኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላት ፡- ለሁላችሁም በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት እና በራሳቸው ስም ምስጋና አቅርበዋል።















የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት 11ኛው የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ






የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት 11ኛው የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት እና የቦርድ ኮሚቴ አባላት በተገኙበት በሂልተን ሆቴል ተካሄደ።

የቦርዱ ስብሰባ አጀንዳዎች የጽህፈት ቤቱን 3ኛ ሩብ አመት ሪፖርት ተወያይቷል።

በተጨማሪም መድረኩ የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት በሸገር ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት አዘጋጅንት በሚካሄደው 13ኛው የልምድ ልውውጥ ዝግጀት ፕሮግራም ላይ የተወያየ ሲሆን የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላት እና ሠራተኞች የቀድሞ የኦሮሚያ ንግድ ቢሮ ኃላፊ የነበሩትንና አሁን የኦሮሚያ መሬት ቢሮ ኃላፊ ሆነው የተሾሙትን ክብርት መሰረትን በመሸኘት አሁን የኦሮሚያ ንግድ ቢሮ ኃላፊ ሆነው ለተሾሙት ክብርት የሺ ጂማ (ዶ/ር) አቀባበል አድርገውላቸዋል።









የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአደንዛዥ እጽ እና ወንጀል ጽሕፈት ቤት (UNODC) ጋር በመተባበር በቢዝነስ ኢንተግሪቲ ላይ ለሦስት ቀናት ሥልጠና ሰጥቷል።



በቢሺፍቱ ከተማ ፒራሚድ ሆቴል የተካሄደው ስልጠና ግልፅነትና ተጠያቂነትን በመለማመድ ተወዳዳሪ መሆን በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ነው።

በመክፈቻ ንግግራቸው የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የኢንፎርሜሽን እና የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ተሾመ ዋቅጅራ ዛሬ በተለዋዋጭ፣ ውስብስብ እና ከፍተኛ ፉክክር ባለው የንግድ አካባቢ ስልጠናው አስፈላጊ መሆኑን ገልቷል።



ተሳታፊዎች ከክፍሎች፣ ከማህበራት እና ከንግዱ ማኅበረሰብ የተውጣጡ ሲሆን ስልጠናው እስከ ኤፕሪል 14 ቀን 2025 ድረስ ተሰጥቷል።

በኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ከሜይ 6-8 -2025 ለሁለት ቀናት በጣሊያን ሬሚኒ ከተማ በሚካሄደው ዓለም አቀፍ ኤክሰፖ ላይ ምርትና አገልግሎቶችን አስተዋወቀ ።

በኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ከሜይ 6-8 -2025 ለሁለት ቀናት በጣሊያን ሬሚኒ ከተማ በሚካሄደው ዓለም አቀፍ ኤክሰፖ ላይ ምርትና አገልግሎቶችን አስተዋወቀ ።



በዚህ ኤክሰፖ የክልል እና የፌዴራል የግብርና ምርቶች፣ እንዱስትሪ ፓርኮች ፣ የኢትዮጵያ ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ባለስልጣን ፣ የግብርና ምርት አምራቾች፣ ላኪዎች እና አስመጪ ድርጅቶች ፣ መንግሰታዊና መንግሰታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች እና ደጋፊዎች ተሳትፈውበታል::



በፕሬዚዳንቱ አቶ ሰብስብ አባፊራ የተመራው ልዑክም ሮም ጣልያን በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤንባሲ ደሚቱ ሀንቢሳ ሮም በሚገኘው ሮም ለሚገኘው የንግድ ልዑክ የክብር እራት ግብዣ የተደረገላቸው ሲሆን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ምስጋናቸውን አቅርበዋል ::







ፕሬዘዳንቱ ለተደረገው መስተንግዶ እና ለክብር እራቱ በራሳቸውና በንግዱ ማህበረሰብ ስም አመስግነው በቀጣይ ኤምባሲው እና ምክር ቤቱ በጋራ ሊያከናውኗቸው በሚችሉ ተግባራት ዙሪያ መመካከራቸውን ገልፀዋል ።

በሌላ በኩል የጣሊያንን የእሁድ ገበያ(Sunday Market) የጎበኙት ፕሬዚዳንቱ መልዕክታቸውንም እንደሚከተለው አስፍረዋል። *በሳምንት አንድ ቀን አቅመ ደካሞች አስቤዛን ጨምሮ ሌሎች ሸቀጦችን ይሸምቱበታል ፤ የኛ አገሩም ጅምሩ መልካም ቢሆንም አሁን ካለው በላይ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል:: ምክንያቱም የገቢ አቅማቸው አነስተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን በእጅጉ የሚያግዝ በመሆኑ።*

ከዚህም ባሻገር የአርሶ አደሮች እና የኢንደስትሪ ምርቶች አቅርቦት ትኩረት ቢሰጠው እንዲሁም የግብይት ሂደቱ ከእሁድ እስከ እሁድ (Sunday to Sunday) እንዳይሆን ጥንቃቄ ቢደረግና የትራፊክ ፍሰቱ አነስተኛ ወደሆነበት አከባቢ ላይ ቢሆን ለውጤታማነቱ አጋዥ ይሆናል እላለው :: የጣሊያን የእሁድ ገበያ ተሞክሮም ይህን ያሳያል ብለዋል።





የኢትዮጵያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ኢኮኖሚያዊ ትስስርን ለማጠናከር የኢትዮጵያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ የቢዝነስ ፎረም በአቡ ዳቢ ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ኢኮኖሚያዊ ትስስርን ለማጠናከር የኢትዮጵያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ የቢዝነስ ፎረም በአቡ ዳቢ ተካሂዷል።

በመድረኩ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤቶች ፌዴሬሽን ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል።



የመግባቢያ ሰነዱን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት ዶክተር ዓይናለም አባይነህ እና የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች አቻቸው ተፈራርመዋል።



ስምምነቱ ንግድን ለማሳደግ፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እና በሁለቱ ሀገራት መካከል ተጨማሪ የንግድ ትስስር ለመፍጠር ያለመ ነው።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዝግጅቱንም የቱሪዝም እና የወጭ ንግድ አቅምን ለማስተዋወቅ፣ የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የንግድና ኢንቨስትመንት ሥራዎች ዕድሎችን እንዲያዩ ማስቻሉም ተጠቁሟል።

የመግባቢያ ስምምነቱ ለንግድ ስራዎች መሳለጥ፣ ለጋራ የትብብር ስራዎች እና እና መረጃ ለመለዋወጥ እንደሚያግዝ ተነስቷል።









6ኛው የ COMFWB የንግድ ትርኢትና ቢዝነስ ኮንፈረንስ በአዲስ አበባ የኢትዮጵያ ስካይላይት ሆቴል ተካሄደ።





ከሚያዝያ 29 እስከ ግንቦት 1/ 2017 የተካሄደው ዝግጅቱ በኮሜሳ የየሴት ነጋዴዎች ፌዴሬሽን (COMFWB) ከኮሜሳ ሴክሬታሪያት እና ከኢትዮጵያ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው።


የዘንድሮው ኮንፈረንስ የሚካሄደው “A Thriving COMESA: Advancing Gender-Responsive Regional Integration for Unlocking Green Investments, Value Chains, Tourism, and Mining in the AfCFTA.” በሚል መሪ ሐሳብ ነው።

ስብሰባው የሴቶችን እና ወጣቶችን በንግድ ስራ ላይ ያለውን ሚና ለማስተዋወቅ ለሽርክና፣ የልምድ ልውውጥ እና በቀጣናዊ ውህደት ውስጥ የተገኙ ስኬቶችን ለመገምገም ዕድሎችን ይፈጥራል። የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የኢትዮጵያ የንግድ ተወካዮችን እንዲሳተፉ በማመቻቸት ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ተሳትፎን ለማረጋገጥ እና ተሳታፊዎች በንግድ ትርኢቱ እና በኮንፈረንሱ ከሚቀርቡት እድሎች ጋር እንዲገናኙ ለማድረግ ምክር ቤቱ ስራዎችን መስራቱንም ጠቁሟል።

ኢትዮጵያ -እስራኤል ቢዝነስ ፎረም በአዲስ አበባ ተካሄደ።

የኢትዮጵያ -እስራኤል ቢዝነስ ፎረም በአዲስ አበባ ተካሄደ።

የረጅም ዘመን ታሪካዊ ግንኙነት ያላቸው ኢትዮጵያ እና እሥራኤል ያላቸውን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሣደግ የሚያሥችል የሁለትዮሽ ቢዝነሥ ለቢዝነሥ ፎረም በአዲስ አበባ ሀያት ሬጀንሲ ሆቴል ነው የተካሄደው።





የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ እና የእስራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒሥትር ጌዲዮን ሳአር በፎረሙ ላይ ተገኝተዋል።

በሌላ በኩል ከኢትዮጵያ ኢንቨሥትመንት ሆልዲንግስ፣ ከኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ኢንቨሥትመንት ኮሚሽን እንዲሁም ከኢንዱሥትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንና የሌሎች ተቋማት ኃላፊዎችና ተወካዮች ተገኝተዋል።



የእሥራኤል አምራቾች ማኅበርና የኤክሥፖርት እና ዓለም አቀፍ ትብብር ሀገራት የተውጣጡ በተለያዩ ዘርፎች ላይ የተሠማሩ ተቋማት እና ኩባንያዎች ኢንሥቲትዩትን ጨምሮ ከሁለቱ በፎረሙ ላይ ተገኝተዋል።

ፎረሙም ሁለቱ ሀገራት ያሏቸውን የቢዝነስ እድሎች ለማየትና ኩባንያዎችም በጋራ መሥራት የሚችሉበትን እድል እንደሚፈጥር ተጠቁሟል።

በተያያዘም የኢትዮጵያ እና እስራኤል ኩባንያዎች የቢዝነስ ለቢዝነስ (B2B) ውይይት ተካሂዷል።

በአዲስ አበባ ሀያት ሬጀንሲ ሆቴል ከተካሄደው የሀገራቱ የቢዝነስ ፎረም ጎን ለጎን የተካሄደው ይህ የቢዝነስ አቻ ለአቻ ውይይት ተቋማት ተቀራርበው ለመሥራትና ልምድ ለመለዋወጥ ትልቅ አጋጣሚ የሚፈጥር ነው ተብሏል።

በውይይቱም ከእሥራኤል የመጡ የሀገሪቱን የአምራቾች ማኅበር ጨምሮ እንደ አልትራ ኢንፎርሜሽን ሶሉሽን፣ ፖስትሮን ኢንጅነሪንግ ያሉ ኩባንያዎች ከኢትዮጵያ አቻዎቻቸው ጋር ተወያይተዋል።









ኩባንያዎቹ መሠል የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይቶች በጋራ ለመሥራትና በሀገራቱ መካከል ያሉትን የገበያ እና ኢንቨሥትመንት አማራጮች በአግባቡ ለመረዳት እንደሚያሥችል ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከፈረንሳይ የልማት ትብብር ተቋም (AFD) ECOTRADE ፕሮጀክት ተወካዮች ጋር ተወያየ።





ሁለቱ አካላት በንግድና ቀጣናዊ ውህደት፣ በእሴት ሰንሰለት ልማት፣ በንግድ ማሳለጥና ማስተዋወቅ፣ በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ነው የተወያዩት።

በኣውሮፓ ኅብረት እና በፈንሳይ የልማት ትብብር ተቋም (AFD) የሚተገበረው « Promoting Ethiopian trade and economic integration through private-led value chains development" ፕሮጀክት በቀጣናዊ የኢኮኖሚ ትስስር፣ በንግድ ማሳደግ እና ቀጣይነት ያለው እድገት ማምጣት፣ በስራ እድል ፈጠራ እና በአካባቢ ልማት በኢትዮጵያ ያሉትን እድሎች በማልማት ላይ እንደሚያተኩር የፕሮጀክቱ ቡድን መሪ ሜሮን ዳኛው ተናግረዋል።





ምክር ቤቱም በፕሮጀክቱ ትግበራ ውጤት ለማምጣት ከግሉ ዘርፍም ሆነ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርን ጨምሮ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በመተባበር እንደሚሰራ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ በውይይቱ ላይ አንስተዋል።

ይህ ECOTRADE የተሰኘው ፕሮጀክት በቅርቡ በይፋ ስራውን ሲጀምር የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነትን ውጤታማ ለማድረግ በተለይም በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ የእሴት ሰንሰለት፣ በአቅም ግንባታ፣ በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነት ማዕቀፍ፣ በፕሮቶኮል፣ ገበያ በህግ ጉዳዮች እና በመሳሰሉት ላይ ውጤታማ ስራ እንደሚሰራ በውይይቱ ተብራርቷል።



ለኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ማኔጅመንት እና ሠራተኞች "የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን ወደ ስኬት መምራት" በሚል ርዕስ ሥልጠና ተሠጠ።

ለኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ማኔጅመንት እና ሠራተኞች "የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን ወደ ስኬት መምራት" በሚል ርዕስ ሥልጠና ተሠጠ።

ስልጠናውን የሠጡት የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሣ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሠር) ሲሆኑ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን ውጤታማ ለማድረግ የለውጥ (Reform) ሥራዎች እየተተገበሩ መሆኑን ገልጸዋል።





እነዚህን የሪፎርም ተግባራት ሥኬታማ ለማድረግ የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በማሣያነት ያነሡት ዋና ጸሐፊው በተለይም በሠው ሐብት አሠተዳደር፣ በጊዜ አጠቃቀም፣ በቅንነትና ታማኝነት ሥለመሆኑ አንሥተዋል፣ ዶክተር ቀነኒሳ ምክር ቤቶች ውጤት

እንዲሁም በትልቁ አቅዶ መሥራትና መተባበር ተገቢ በተለያዩ የአመራር ሞዴሎች ዙሪያ ማብራሪያ የሠጡት ተኮር ተግባራትን ያከናውኑ ዘንድ የሥኬታማ አመራር መርሆችን መከተል እንደሚገባቸው አንሥተዋል።





ምክር ቤቱ የሚተገብራቸው የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ መሠረታዊ የቻምበር መርሆችንና አሠራሮችን በአግባቡ መተግበር ያሥፈልጋል ብለዋል።

የምክር ቤቶችን የአሠራር ሂደቶችን በመከተል፣ እርስ በርስ በመደጋገፍ፣ የሠለጠነና በቴክኖሎጂ የታገዙ ሥራዎችን በማከናወን ሠራተኞች ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸውም ተነሥቷል።

ምክር ቤቱ ለግሉ ዘርፍ ተሠሚነት ያለው ድምጽ እንዲሆን ከምንጊዜውም በበለጠ ከአባላት ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር፣ በምርምርና አድቮኬሲ ፣ በሥልጠናና በሌሎችም መሥኮች ከመንግሥትና ከልማት አጋሮች ጋር የሚሠሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንደሚገባቸውም ተነሥቷል።

ከሀገር ውሥጥ ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የቢዝነስ እንቅስቃሴ በአግባቡ በመረዳት በንግድና ኢንቨሥትመንት ፕሮሞሽን ዙሪያ ሀገራዊ ለውጥ ለማምጣትም የተጠናከሩ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑም ተጠቁሟል።





መሠል ሥልጠናዎች የማኔጅመንት እና የሠራተኛውን ግንኙነት በማጠናከር ውጤታማ ሥራ ለመሥራት እንደሚያግዙ ሠልጣኞቹ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት



የአሁን ገጽታ





የግሉ ዘርፍ ድምጽ!



Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

The Center's Services

- ⇒ **Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services**
- ⇒ **Internet & Electronic Resource Services**
- ⇒ **Support on information searching**
- ⇒ **Reprographic Service**
- ⇒ **Advising users on reference materials available in resource center.**
- ⇒ **Types of Materials in the Center**
- ⇒ **Books, Periodicals, Journals, Magazines**
- ⇒ **Audio and Video CD collections**
- ⇒ **E-Books & Publications**
- ⇒ **Business & Economic Statistics & Databases**
- ⇒ **Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)**

For further information:

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations ECCSA Resource & WTO Reference Center

- ⇒ **Mexico Square, ECCSA Building**
- ⇒ **Ground Office , Room No. 13/14**
- ⇒ **Open to public Monday-Friday from 2:30 am to 5:00 pm**
- ⇒ **Tel: 251-115514005**
- ⇒ **Mob. 0966038499**
- ⇒ **Fax: 251-115517699**

ዋና አዘጋጅ፡-

ተሾመ ዋቅጂራ

ም/ዋና አዘጋጅ፡-

ደበበ አበበ

አዘጋጅ

ስማቸው ተበጀ

ፎቶግራፍ

ያለምፍሬ በቀለ

FOLLOW US ON

www.ethiopianchamber.com

t.me/ethiopiachamber

facebook.com/EthiopianChamber

youtube.com/@ethiopianchamber

twitter.com/EthiopiaChamber

info@ethiopianchamber.com

+251115514005

